

# እማማ ኢትዮጵያ!!!!

## ከማተቤ መለሰ ተሰማ

ሃገሬ ሃብቴ ነሽ ጥሪቴ፣
የአባቶቸ ውርስ ማንነቴ፣
ሁለመናየነሽ እናቴ።
ውብ አየርሽ ሲናፍቀኝ፣
ማነው እሱ ከትዝታሽ የሚያርቀኝ፣
የእኔ እነትሽን የሚነጥቀኝ።
በስደት ብኖር ከምር ብገፋ፣
ብንሳቆልም ብከፋ፣
ፍቅርሽ ከውሰጤ አይጠፋ።
አዎ!! ሺጊዜ ወድቄ ብነሳ፣
መቸም አንችን አልረሳ፣
ምንም ቢበዛብኝ አበሳ።
ኢትዮጵያ እንዴት አድርጌ ልዘንጋሽ፣
ውስጤ ሠርጿል ጺጋሽ፣
በምን ይመዘናል ዋጋሽ?
ያለሀገሬ አይታወቅም ማንነቴ፣
መመኪያየ ነሽ ኢተዮጵያ እናቴ፣
ክብሪ ሞገሴ ኩራቴ።
ያነች ችግኝ ነኝ ያጸደቀሽኝ፣
አቅፈሽ ደግፈሽ ያሳደግሽኝ፣
አንደላቅቀሽ ያኖርሽኝ።
ከሸት ካዝመራሽ ተመግቤ፣
መልካም አየርሽን ጠግቤ።
በእንቁ በወርቅሽ አምሪ፣
ኖሪያለሁ ባንች ከብሪ።
መቸም አረሳው ውለታሽን፣
የእናትነት ፍቅርሽን።
አዎ!!አልረሳውም እናታለም፣
አለሽ በውስጤ ለዘላለም።

እኖራለሁኝ እንዲህ ናፍቄ፣
ፍቅርሽን በውስጤ ሰንቄ።
አካልሽ አካሌነው ልንገርሽ፣
ከምር ያመኛል ሲነኩሽ።
በአባቶቻችን ደም ተጠምቆ፣
የኖረው አንችነትሽ ደምቆ።
ዛሪ እንዲህ ሲዋረድ በባንዳ፣
ዝም ብየ በማየቴ አለብኝ ከፍየ የማልጨርሰው እዳ።
ኢትዮጵያ!እማማየ! ሀገሪ፣
አልረሳሽም እስከ ግባተ መቃብሪ፣
አልረሳሽም እስከ ግባተ መቃብሪ።
ማተቤ መለሰ ተሰማ

ኢሜልmatebemelese@yahoo.com